# ወርሃዊ የአየር ጠባይ ትንበያ መጽሔት

## ከፌብርዋሪ 1-28/2021 የአየር ጠባይ ግምገማ

## ከማርች 1-31/2021 የአየር ጠባይ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ማርች 2021
አዲስ አበባ

| ርዕስ | ገፅ |
|---|---|


እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 28/2021 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ ...................... Error! Bookmark not defined.

ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 28/2021 ድረስ የነበረው ..........................................................................
የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ............................................................................ Error! Bookmark not defined.

ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 28/2021 ድረስ ዝናብ ..............................................................................
የዘነበባቸው ቀናት ብዛት ......................................................................... Error! Bookmark not defined.

ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 28/2021 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛሲነፃፀር ............................................................................................ Error! Bookmark not defined.

እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 28/2021 የነበረው የአየር ጠባይ በግብርናው እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖError! Bookmark not defined.

ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 28/2021 ድረስ የነበረው ..........................................................................
የእርጥበት ሁኔታ ................................................................................... Error! Bookmark not defined.

እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 28/2021 የነበረው የአየር ጠባይ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ......................................................................................................................... Error! Bookmark not defined.

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 28/2021 ድረስ የነበረው ..........................................................................
የእርጥበት ሁኔታ ................................................................................... Error! Bookmark not defined.

እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 31/2021 የሚኖረው የአየርጠባይ አዝማሚያ ...................... Error! Bookmark not defined.

እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 31/2021 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ................................................................................ Error! Bookmark not defined.

እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 31/2021 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ................................................................................ Error! Bookmark not defined.


## እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 28/2021 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ

ባለፈዉ የፌብርዋሪ ወር ለዝናብ መኖር አመቺ ሁኔታን የሚፈጥሩ የአየር ሁኔታ ክስተቶች በሰሜን ምስራቅ፣ በመካከለኛዉ፣ በደቡብ ምዕራብና ደቡብ ደጋማ ስፍራዎች ላይ የተሻለ ገጽታ ነበራቸዉ፡፡ በተለይም በስምጥ ሸለቆና አጎራባች በሆኑ ቦታዎች ላይ ይበልጥ ከመጠናከራቸዉ ጋር በተያያዘ በሁለተኛዉ አስር ቀናት የመጨረሻዉቹ እና ሶስተኛዉ አስር ቀናት መጀመሪያዎቹ ጥቂት ቀናት ላይ በአንዳንድ የደቡብ ምዕራብ አካባቢዎች ላይ ከባድ ዝናብ እንዲኖር አስተዋፅኦ አድርጓል፡፡ በአጠቃላይ ባለፈዉ የፌብርዋሪ ወር በመካከለኛዉና ምስራቅ አማራ፣ በምዕራብ፣ በመካከለኛዉና ጥቂት የደቡብ ኦሮሚያ፣ በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች እንዲሁም በሲዳማ ክልል አካባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ ዝናብ የተመዘገበ ሲሆን፤ አልፎ አልፎ ከነበረዉ ጠንካራ የደመና ክምችት በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች እንዲሁም በምዕራብ ኦሮሚያ ጥቂት ቦታዎች ላይ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡


ባለፈዉ የፌብርዋሪ ወር የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም በቤንች ማጂ፣ በደቡብ ኦሞ፣ በጋሞ፣ በጎፋ፣ በወላይታ፣ በዳዉሮ፣ በሸካ፣ በከፋ፣ በሀዲያ፣ ስልጤና ጉራጌ፣ በሰሜንና ደቡብ ወሎ ዞኖች ላይ ከ25-116 ሚሜ የሚደርስ ከ4-8 ቀናት ያህል ዝናብ የነበራቸዉ ሲሆን፤ በምስራቅና ደቡብ ትግራይ፣ በዋግህምራ፣ በደቡብ ጎንደር፣ በምስራቅ ጎጃም፣ በሰሜን ሸዋ(03)፣ ከአፋር ክልል ዞን 02፣ 04፣ 05ና 03፣ ከኦሮሚያ ክልል በአብዛኛዉ የሸዋ ዞኖች ላይ፣ በጅማና ምስራቅ ወለጋ፣ በአርሲና በባሌ፣ በጥቂት የጉጂና ቦረና ዞኖች እንዲሁም በሲዳማ ክልል ዞኖች ላይ ከ5-25 ሚሜ የሚደርስ ከሶስት ላነሱ ቀናት ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 6 እና 7)፡፡

ባለፈዉ የፌብርዋሪ ወር የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር በምስራቅና ደቡብ ትግራይ፣ በዋግህምራ፣ በደቡብ ጎንደር፣ በምስራቅ ጎጃም፣ በጥቂት የሰሜንና ደቡብ ወሎ እንዲሁም ሰሜን ሸዋ (03) ፤ በጅማ፣ በጥቂት የምስራቅ ወለጋና ሰሜን ሸዋ (04)፣ በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ከሞላ ጎደል ሁሉም ዞኖች ላይ መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ ተመዝግቧል (ካርታ 8)፡፡


ካርታ 6 ከፌብርዋሪ 1 እስከ 28/2021 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 7   ከፌብርዋሪ 1 እስከ 28/2021 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት



ካርታ 8 ከፌብርዋሪ 1 እስከ 28/2021 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር







ከመደበኛ በታች መደበኛ ከመደበኛ በላይ

## እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 28/2021 የነበረው የአየር ጠባይ በእርሻ ሥራ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፈዉ የፌብሪዋሪ ወር 2021 የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ሲገመገም በሁለተኛዉ እና በሶስተኛዉ አስር ቀናት በመካከለኛዉና ምስራቅ አማራ፣ በምዕራብ፣ በመካከለኛዉና ጥቂት የደቡብ ኦሮሚያ፣ በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች እንዲሁም በሲዳማ ክልል አካባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ ዝናብ የተመዘገበ ሲሆን፤ በተለይም የበልግ ሰብል አብቃይ በሆኑት አካባቢዎች የተሻለ የእርጥበት ገጽታ እንደነበራቸው የተነተኑ የግብርና ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመለክታሉ። ይህም የተገኘው እርጥበት የበልግ ሰብል በስፋት አምራች ለሆኑት የሀገሪቱ አካባቢዎች የማሳ ዝግጅት ለማድረግና የዘር ስራ ለማከናወን አዎንታዊ ሚና ነበረው፤ በተጨማሪም ለቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት ከነበረው አስተዋፅዎ ጎን ለጎን ለመጠጥ ውሃና ለግጦሽ ሳር አቅርቦት የጎላ ሚና ነበረው። እንድሁም አልፎ አልፎ ከነበረዉ ጠንካራ የደመና ክምችት በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች እና በምዕራብ ኦሮሚያ ጥቂት ቦታዎች ላይ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ የተመዘገበ ሲሆን፤ ይህም ሁኔታ የበልግ እርሻን ለሚያከናውኑ አካባቢዎች የማሳ ዝግጅትና ለዘር ጊዜ የእርሻ ስራ እንቅስቃሴ እንዲሁም ለአርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች ለመጠጥ ውሀ፤ ለግጦሽ ሳር አቅርቦትና ለቋሚ ሰብሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት የጎላ ጠቀሜታ ነበረው፡፡ በሌላ በኩል በተለይም በቆላማ አካባቢዎች ላይ የተስተዋለው ከፍተኛ ሙቀት አፈር ውስጥ የሚገኘውን እርጥበት እንዲቀንስ ከማድረግም ሆነ ከእንስሳት ጤንነትና አመጋገብ አንፃር የተወሰነ አሉታዊ ጎን ነበረው (ካርታ 9) ።


ካርታ 9 ከፌብርዋሪ 1 እስከ 28/2021 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ


14
12
10
8
6
4
34
36
38
40
42
44
46
48
እጅግ በጣም እርጥብ
በጣም እርጥብ
እርጥብ
ከፊል ደረቅ
ደረቅ
በጣም ደረቅ

## ኢ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስለ 31/2021 የነበረው የአየር ጠባይ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ኢ.ኤ.አ 1-28 ፈብሪዋሪ 2021 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረውን ተፅዕኖ በተመለከተ በጥቂት የመካከለኛዉ ኦሞ ጊቤና ስምጥ ሸለቆ እንዲሁም የመካከለኛዉ አባይ እና አዋሽ ኪስ ቦታዎች ከመጠነኛ እርጥበት እስከ እርጥበታማ ሁኔታ ነበሩ፡፡ በሌላ በኩል የተቀሩት ተፋሰሶች ከፊል ደረቅ እና ደረቃማ ሁኔታ ተፅዕኖ ስር ነበሩ (ካርታ 10) ፡፡

ካርታ 10 ኢ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 28/2021 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



## እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 31/2021 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ

በመደበኛ ሁኔታ ከቀደመው ወር በተሻለ ሁኔታ በማርች ወር የበልግ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች መደበኛ ቦታዎቻቸውን እየያዙና እየተጠናከሩ የሚሄዱበት ጊዜ ሲሆን፤ በተለይም በበልግ አብቃይ አካባቢዎች ላይ ከሚፈጠሩ ጠንካራ የደመና ክምችቶች በመጠንም ሆነ በሥርጭት የተሻለ ዝናብ ይኖራል።

በሚቀጥለው ወር ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በአብዛኛው እየተጠናከሩ ሊሄዱ እንደሚችሉ የሚጠበቅ ሲሆን በተለይም የሰሜን ምስራቅ፣ የመካከለኛዉና የደቡብ የአገሪቱ ክፍልች በአብዛኛዉ ከመደበኛዉ ጋር የተቀራረበ ዝናብ ሊያገኙ እንደሚችል የሚጠበቅ ቢሆንም፤ አልፎ አልፎ ደረቃማ የአየር ቀናት ሊዘወተሩ እንደሚችሉ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በሌላ በኩል በተለይም በዝቅተኛ ቦታዎችና በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን እንደሚጨምር ይጠበቃል፡፡

<u>በአጠቃላይ በሚቀጥለው ወር ከኦሮሚያ ክልል ጅማ፣ የምዕራብና ቄለም ወለጋ፣ የአርሲና ባሌ ዞኖች፣ የቦረናና የጉጂ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል ሰሜንና ደቡብ ወሎ፣ ሰሜን ሸዋ፣ ምዕራብና ምሥራቅ ጎጃም እና ሰሜንና ደቡብ ጎንደር፤ ከጋምቤላ ክልል የመዠንግ ዞን፤ ከደቡብ ብሄር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል የከፋ፣ የሸካ፣ የቤንች ማጂ፣ የሰገን ህዝቦች እንዲሁም የዳዉሮና ኮንታ ዞኖች በአብዛኛው ከመደበኛ ጋር የተቀራረበ ዝናብ እንደሚኖራቸው ይጠበቃል። የተቀሩት የሀገሪቱ አካባቢዎች በአመዛኙ ደረቅ ሆነው ይሰነብታሉ።</u>

## እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 31/2021 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በመደበኛ ሁኔታ የማርች ወር የወቅቱ እርጥበት በጊዜም ሆነ በቦታ አንፃራዊ በሆነ መልኩ እየተጠናከረ የሚሄድበት ጊዜ ነው። ከዚህም ጋር ተያይዞ የበልግ ሰብል አምራች የሆኑት አካባቢዎች በስፋት ዘር የሚዘሩበትና የማሳ ዝግጅት የሚያከናውኑበት ወቅት ሲሆን፤ በተለይም የሰሜን ምሥራቅ፣ የምሥራቅ፣ የደቡብና የደቡብ ምሥራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች በመጠንም ሆነ በሥርጭት የተጠናከረ እርጥበት የሚያገኙበት ጊዜ ነው።

በተሰጠው የአየር ሁኔታ ትንበያ መሰረት በሚቀጥለው የማርች ወር የእርጥበት ሁኔታው በአብዛኛው ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረና እየተጠናከረ እንደሚሄድና ከዚሁ ጋር ተያይዞም አብዛኛዎቹ የበልግ ሰብል አምራች የሆኑት አካባቢዎች በተለይም የሰሜን ምስራቅ፣ የመካከለኛዉና የደቡብ የአገሪቱ ክፍሎች በአብዛኛዉ ከመደበኛዉ ጋር የተቀራረበ ዝናብ ሊያገኙ እንደሚችል ይጠበቃል፡፡ ይህም የሚጠበቀው እርጥበት የበልግ እርሻ ስራ እንቅስቃሴ እያካሄዱ ላሉ አካባቢዎች ለሰብሉ የውሃ ፍላጎት መሟላት፣ የረጅም ጊዜ የመኸር ሰብሎችን ቀድመው ለሚዘሩ አካባቢዎች የማሳ ዝግጅትና ለዘር ጊዜ የእርሻ ስራ እንቅስቃሴ፣ ለቋሚ ሰብሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት እንዲሁም ለአርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለመጠጥ ውሀና ለግጦሽ ሳር አቅርቦት ጠቀሜታ እንደሚኖረው ይጠበቃል። በሌላ በኩል በአንዳንድ የበልግ ተጠቃሚ ቦታዎች ላይ አልፎ አልፎ ሊዘወተር እንደሚችል በሚጠበቀው ደረቃማ ቀናት መክንያት በበልግ እርሻ እንቅስቃሴ ላይ ሊከሰት የሚችለውን አሉታዊ ተፅዕኖ ለመቀነስ የተገኘውን እርጥበት በአግባቡ በመያዝና በመጠቀም እንዲሁም እንደ አካባቢው ሁኔታ የውሃ እቀባ ስራዎችን መስራትና መጠቀም ይኖርባቸዋል፡፡

## እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 31/2021 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በውሀው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በማርች ወር በአብዛኛዎቹ የበልግ እርጥበት ተጠቃሚ ተፋሰሶች ላይ እየተጠናከሩ ሊሄዱ እንደሚችሉ የሚጠበቅ ሲሆን፤ በተለይም የሰሜን ምስራቅ፣ የመካከለኛዉና የደቡብ የአገሪቱ ተፋሰሶች ላይ በአብዛኛዉ መጥነኛ የእርጥበት መጠን ሊያገኙ እንደሚችል የሚጠበቅ ሲሆን፤ በሌላ በኩል የተራዘመ ደረቅ ሰሞን ከሙቀት መጨመር ጋር በአመዛኙ እንደሚኖር የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ የላይኛው ባሮአኮቦ፣ አዋሽና ዋቢሸበሌ፣ ደቡባዊና ምስራቃዊ መካከለኛ አባይ፣ የላይኛውና የመካከለኛው ስምጥሸለቆ፣ ኦሞጊቤ፣ ገናሌዳዋ፣ እንዲሁም በጥቂት የላይኛው ተከዜ ተፋሰሶች ላይ አነስተኛ የእርጥበት መጠን እንደሚያገኙ ይጠበቃል፡፡ በተጨማሪም በዚህ ወቅት የቀኑ የሙቀት መጠን መጨመር ጋር ተያይዞ በውሃ አካላት ላይ ከፍተኛ የትንተ መጠን የሚኖርበት ወቅት በመሆኑ የውሃ አጠቃቀማችን ለብክነት የሚያጋልጥ ሊሆን እንደሚገባው እንመክራለን፡፡